

# የኢየሱስ መመረመር

ወታደሮች ኢየሱስን ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ወሰዱት። በዚያም ተመረመረ። ካህናቱና ገዢዎች ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ማለቱ ወንጀለኛ ያደርዋል በሚለው ጉዳይ ተስማምተዋል። ለዚህም ምክንያቱ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ አያምኑም ነበርና ነው። ኢየሱስ መሞት እንዳለበት ሁሉም ተስማምተው ነበር።

ሆኖም በሮማን ሕግ መሠረት አይሁዳውያን ማንንም ሰው በሞት መቅጣት አይችሉም ነበር። ስለዚህ ኢየሱስን ወደ ሮማዊው ገዢ ወደ ጲላጦስ ወሰዱት። ጲላጦስ ግን ኢየሱስን በሞት የሚቀጣበትን ምክንያት አላገኘም። ስለዚህ የአይሁድን መሪዎች በኢየሱስ ላይ የወደዱትን እንዲያደርጉበት ነገራቸው።

ወታደሮቹ በኢየሱስ ላይ አላገጡበት። ኢየሱስን “የአይሁድ ንጉስ” እያሉ አሾፉበት። ኢየሱስ ንጉስ እንደሆነ ግን አያምኑም ነበር። በራሱ ላይ የእሾህ አክሊል አስቀመጡ። በእጁም በትር አስያዙት። ቀይ ካባን አልብሰውም ተፉበት። ከዚያም ገረፉት።

*ይህ ታሪክ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 26: 47-67 እና በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 27:11-26 ውስጥ ይገኛል።*